# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅድስ አሐዱ አምላክ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ግንቦት 30 ቀን፡ 2012 ዓ.ም.

nigatuasteraye@gmail.com

## ውድነሽ አምሳሉ በፍቅር እስከመቃብር

"ብኪ ወልድየ ሳዕለ ዘሞተ ወላህወ ወአህምም ርእሰከ ወበከመ ግዕዙ  ግበር ሎቱ ተዝካሮ ወኢተጸመም ሞቶ ለዘተልእከከ" (ሲራክ 38 ፡16)

"በህይወት እያለ ያገልግሎት ውለታ ለሰጠህ ወገን አልቅስለት መታሰቢያውን ለመግለጽ አትርሳ"



## ወይዘሮ ውድነሽ አምሳሉ

የወይዘሮ ውድነሽን ሞት ከሊቀ ማእምራን ዶ/ር አማረ ከሰማሁባት ቅጽበት ጀምሮ ብዙ የተደራረቡ ትዝታወች እርስ በርሳቸው እየተጓተቱ መጡብኝ። ከታላቁ አባታቸውና ከመሳሰሉት ሊቃውንት ወይዘሮ ውድነሽ ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያና፤ ስለ ቤተ ክርስቲያንችን የሰሙትን ይነግሩኝ የነበረው ሁሉ መጣብኝ።  በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፋቸው *"ከብዙ ስርዝና ድልዝ ጋራ የጻፍኩትን የመጀመሪያውን ረቂቅ በብዙ ትጋትና ጥንቃቄ እንደገና ደህና አርጋ ባትጽፍልኝ ኖሮ ብዙ  ችግር ይገጥመኝ ስለነበረ ውለታዋን አልረሳውም"* ብለው ክቡር ዶ/ር አቶ አዲስ ዓለማየሁ የተናገሩላቸው ወይዘሮ ውድነሽ አምሳሉ ማርያም እንተ እፍረትንና ፌቤንንም አስታወሱኝ።

ማርያም  (እንተ እፍረት)  እንድትታወስ የተነገረባትን ወንጌልንና ፌቤን እንድትታወስ የተነገረባትን መልእክት በእኩልነት እንደማናየቸው፤ ወይዘሮ ውድነሽ እንዲታወሱ የተነገረባት ፍቅር እስከ መቃብርን  ከሁለቱም ቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ አናነጻጽርም። ይሁን እንጂ ማርያምንና ፌቤንን እንዲወሱ ያደረጋቸውን አገልግሎት ከወይዘሮ ውድነሽን  አገልግሎት ጋራ ብናመሳሰለው የምሳሌነቱ እርከን ብዙ የሚራራቅ አይመስለኝም።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማርያም እንተ እፍረትን በወንጌሉ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ፌቤን በመልእክቱ እንዲታወሱ ከፈቀዱላቸው፡-  ስርዝ ድልዝ  (ራሳቸው እንዳሉት) የእጅ ጽሑፍ አስተካክለው በመጻፍ  ክቡር አቶ አዲስን  ያገለገሏቸውን፤ ይልቁንም እኛን በአካልና በቃል ያገለገሉንን እናታችን ወይዘሮ ውድነሽን   በዚህች ጦማር ብናስታውሳቸው  የማይስማማው ይኖራሉ ብየ አላስብም።

ወንጌሉን የሚያነብ ማርያም እንተ እፍረትን፤ የሮሜን መልእክት የሚያነብ ፌቤንን፤ እንደሚያስታውስ ፍቅር እስከመቃብርን የሚያነብም ወይዘሮ ውድነሽን እንዲያስታውስ አርባቸውን ምክንያት በማድረግ ይህችን ጦማር በ 5 ከፍየ አቀረብኳት።

*ሀ. ወይዘሮ ውድነሽን በግሌ ሳስባቸው*

ለ. ወይዘሮ ውድነሽ በክቡር ዶ/ር አቶ አዲስ ዓለማየሁ እይታ

ሐ. ወይዘሮ ውድነሽ አምሳሉ በፍቅር እስከመቃብር

መ. ወይዘሮ ውድነሽ በዶ/ር ዓቢይ ፈቃጅነት በተፈጸመው የሲኖዶሱ እርቅ

ሠ. የወይዘሮ ውድነሽ ሞት ያስከተለብኝ እዳወች

## ሀ. ወይዘሮ ውድነሽ በግሌ ሳስባቸው

የወይዘሮ ውድነሽን ሞት ከሊቀ ማእምራን ዶ/ር አማረ ከሰማሁባት ቅጽበት ጀምሮ፤ ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ ታሉቁ ከአባታቸውና ይመስሏቸው ከነበሩት ሊቃውንት ሲያዩትና ሲሰሙት የነበረውንና ክቡር ዶክተር አዲስ ዓለማየሁ በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፋቸው አማካይነት እያነሱ ይነግሩኝ የነበረው ቀን ሌላ እንዳላስብ ሌት እንዳልተኛ አደረገኝ።

ትላንትም ዛሬም ለሀገርና ለወገን ቁም ነገር በመስራት ላይ ያሉትንና ነገም ወደፊት የሚሰሩትን ኢትዮጵያውያት ሴቶች የምንቃኝባቸው የምንለካባቸውና የምንመዝንባቸው እናታችን ወይዘሮ ውድነሽ ይህች ዓለም በሞት ከተለዩዋት አርባ ቀናት ሆኗት።

“ወንሕነኒ ናፍጥን ከመ ነህሉ ውስተ ሃይማኖት ርትእት ወበከመ ጽሑፍ ወንሥራዕ አልባቢነ ከመ ንተሉ ስብሀተ ርቱዐ ዘረከቡ ዕልክቱ” (ሃይ ም 74፡7) ማለትም፡- እናታችን የተጠመቁባትን እምነት ከወላጆቻቸው የተማሩትን ስርአት የኢትዮጵያውነትን ኩነት ጠብቀው ይህችን ዓለም ለቀው ተለይተውን በመሄዳቸው የኛም ጥላ ከተገፈፈብን **አርባ ቀናት** ሆኑን ።

ጠቢቡ ሲራክ “ብኪ ወልድየ ላዕለ ዘሞተ ወላህወ ወአህምም ርእሰከ ወበከመ ግዕዙ ግበር ሎቱ ተዝካሮ ወኢተጸመም ሞቶ ለዘተልእከከ” (ሲራክ 38 ፡16) እንዳለው፡- ልጅ ቤተ ሰብ ዘመድ አዝማድና ወዳጅ በሞት ለተለየው ወገኑ ያለቅስለታል። ተዝካር ያወጣለታል። ለእናታችን ወይዘሮ ውድነሽ የሚያለቅሱላቸው ተዝካራቸውን የሚያወጡላቸው በሥጋ የወለዷቸው ዘመድ አዝማድ አሏቸው። በመንፈስ የወለዷቸውም ብዙ ሴቶችም ወንዶችም አሏቸው።

በመንፈስ ከወለዷቸው ወንዶች ልጆቻቸው አንዱ በመሆኔ፤ ለተዝካራቸው ሌማት (ሌማት ማለት በጎጃም አማራ ባህል ለተዝካርም ሆነ ለሰርግ በሚደገስ ድግስ የቅርብ ዘመድ በተሳትፎ የሚያቀርበው ድግስ ) ድርሻየን ለመወጣት ወሰንኩ። ድርሻየን ስፈትሽ “ግበር ሎቱ ተዝካሮ ወኢተጸመም ሞቶ ለዘተልእከከ” ማለትም፡- ያገለገለህን ሰው አስበው ከሚለው ከጠቢቡ ሲራክና **“ውለታዋን አልረሳውም”** ብለው ክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁ ከተናገሩት፤ ወይዘሮ ውድነሽን የማያስረሳ ትዝታ መጻፍ ሆኖ አገኘሁት።

በዚህ ሁሉ ተደራራቢ ግፊት ወይዘሮ ውድነሽን ሳስብ በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ የተዳሰሱትን እነ ሰብለን፡ እነ በዛብህን፡ እነ ጉዱ ካሣን፤ እነ ፍታውራሪ መሸሻንና አበጀ በለውን በዓይነ

ህሊናየ እንዳያቸው አደረገኝ። በነ ቄስ ሞገሴ የነበረው ደካማ ቅስና፤ በነ አባ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ የነበረው በዓለም እየኖሩ ምነና ፤ አባ ዓለም ለምኔ ከዓለም ጋራ የነበራቸው ፍጹም የመቆራረጥ ምንኩስና፤ የአለቃ በላይ ቀጥ ያለ የሊቅነት አቋም የዛሬወቹን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንና የኢትዮጵያ አገራችን ሁለንተና አየሁት።

ኢትዮጵያ ከተመሰረተችበት ዘመን ጀምሮ የተነሱባት ጠላቶች ፤ ጣሊያንም ጭምር፡ በኢትዮጵያና በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሰሩትን ስህተት ጥፋትና መከራ ኢህአዴግ ከየስርቻው እየፈለገ አባዝቶና ደምሮ በኢትዮጵያ ላይ የከመረውን መከራና ስቃይ ከስር ስቅስቅ አርጎ ወደላይ አጉኖ አሳየኝ። በሕይወተ ሥጋ ያሉት እነ ቴዲ አፍሮና ሌሎችም ያቀረቧቸው ቅላጼዎች <u>በጣሊያን ወረራ</u> ጊዜ እነሽፈራው እነ በላይ ዘለቀ እነፍታውራሪ ተሰማ ላቀው በነማይ በብቻና በለምጨን በበረንታ በሸበል አንጎራጎሩት እየተባለ ስሰማው ያደኩት፡-

“አጌጉረውና እርጥቡን ከደረቅ

እዚያው ጤሶ ጤሶ እዚያው ነዶ ይለቅ” የሚባለው እንጉርጉሮ ትውስ አለኝ።

በዚያን ጊዜ በነ ሽመልስ ለገሰ ይመራ የነበረው የዲሲ ግብረ ኃይል፡ ጸሐፊወች፡ ጋዜጠኞችና አንጎራጓሪወች የሰበቁት የሰላም ዘንግ፡ የነቀነቁት የመረጋጋት ዘገር፡ የታጠቁት የአርብኝነት ዝናር፡ያሰሙት ወኔና ስሜት ቀስቃሽ ቅላጼያቸውን ወይዘሮ ውድነሽ እያወሱ ይገልጹልኝ የነበረው አድናቆት፡ በሕዝቡ ሕሊና ታምቆ ከነበረው ስሜት ጋራ የኔንም ደምሮ የቀሰቀሰበት ወቅት ውል ብሎ ታየኝ። ስሜቱ የተቀሰቀሰበት የኢትዮጵያ ህዝብ፡ የአንበሳ ግርማ ተላብሶ፡ የነብር ቁጣ ተንተርሶ፡ በጎንደር፡ በአዲስ አበባ ና በባህርዳር የዘፈነውን፡ የዘመረውንና ያረገደውን በአካላዊ ህሊናየ አሁንም እንዳየው አደረገኝ። በከፋም በደግም ኢትዮጵያንና ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን የሚነካካ ነገር ስሰማና ሳይ፡ ከማነጋግራቸውና ከሚያነጋግሩኝ አንዷ የነበሩት የወይዘሮ ውድነሽን ሞት ስሰማ በዚህ ሁሉ ማእበላዊ ትዝታ ውስጥ ገባሁ።

የሚያሳስብ ነገር በሀገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ መድረሱን ሰምቼ በሀሳብ ማእበል ውስጥ ስገባ፤ ከማነባቸው መጻሕፍት ውጭ፤ ምክር ሀሳብና መጽናናት ከሚለግሱኝ ድምጻቸው ሲዘገይብኝ ከምፈልጋቸውና የኔም ድምጽ ሲዘገይባቸው ከሚፈልጉኝ አረጋውያን አባቶቼና መምህሮች አንዱ አቡነ መቃርዮስ በዚህ ማእበላዊ ትዝታ ውስጥ ሳለሁ ደወሉልኝ። (አቡነ መቃርዮስ ቀድሞ አባ ጴጥሮስ ገ/ሥላሴ በመባል የሚታወቁት ኤርትራዊው ናቸው) ።

“ምነው ድምጽህ ጠፋ? አንተም፡ ምእመናኑም፡ በቅርብና በሩቅ ያሉ ወገኖቻችንስ እንዴት ናችሁ ?ብለው ጠየቁኝ። “ሲጠፉብኝ ከምፈልጋቸው፡ ስጠፋባቸው እየጸለዩልኝ ከሚፈልጉኝ እናቶቼ አንዷ ወይዘሮ ውድነሽ ማረፋቸውን ሰምቼ፡ ብዙ ትዝታወች ቀስቅሰውብኝ በሀዘን በትካዜ እና በሰመመን ላይ ነኝ” አልኳቸው። “በዘመኑ ወረርሽኝ ነው? ወይስ በሌላ ደዌና በእርግና ተጽእኖ ነው? አሉና ጠየቁኝ። “በሌላ ደዌና በእርግና ተጽእኖ ነው” አልኳቸው። “ማን ይባላሉ? ” ብለው ጠየቁኝ።

ቀጥታ ስለወይዘሮ ውድነሽ ከመናገር ይልቅ፡ በክቡር ዶክተር አቶ አዲስ ዓለማየሁ በኩል ወይዘሮ ውድነሽን ብገልጽላቸው ፈጥነው ይረዱኛል ብየ በመገመት “ክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁን ያውቋቸው ኑሯል ? ብየ ጠየኳቸው።

”እሳቸውንማ ! እንኳን እኔና በኔ ዘመን ያለ ፡ ክርስቶስ ሲመለስ በምድር ላይ የሚያገኘው በዓለም ፍጻሜ ጫፍ ላይ የሚኖረው ትውልድ የሚረሳቸው አይደሉም“ አሉኝ። ክቡር አቶ አዲስ የጻፉትን ፍቅር

እስከ መቃብር የሚባለውን መጽሐፍ ያስታውሳሉ? አልኳቸው። ክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁን ስጠቅስላቸው፡ በውስጣቸው የተዳፈነው የአቶ አዲስ ዓለማየሁ ትዝታ የሳቧትን ትንፋሽ እስኪውጧት ድርስ ሳይገልጹ እንዲዘገዩ ፋታ አልሰጠቻቸውም። አቡነ መቃርዮስ የኃያሉን የክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁን ያርበኝነት መንፈስ የገለጹበት አድናቆት፡ ወይዘሮ ውድነሽን እንዳይ ከተራራ ጫፍ ላይ ያወጣኝ መሰለኝ።

## ለ. ወይዘሮ ውድነሽ በክቡር ዶክተር አቶ አዲስ ዓለማየሁ እይታ

በስሜታዊ አገላለጻቸው "ስለፊደሎች አጠቃቀም የሰነዘሩበት ሀሳብ ባይስማማኝም፡ ፍቅር እስከ መቃብርማ ከሳቸው በፊት፡ በሳቸው ጊዜና ከሳቸው ወዲህ የተነሱ ጸሐፊወች ለጻፏቸው መጻሕፍት ሚዛን ነው" ከአሉኝ በኋላ፡- አቡነ መቃርዮስ ቀጠሉና፡-"አቶ አዲስ ቢያልፉም፡- ሊቅነትን ከአርበኝነት፡ መንፈሳዊነትን ከስነ ልቡና፡ ታማኝነትን ከስነ ምግባር ጋራ አጣምረው፡ ሳይዘነፍባቸው በሰሩት ስራ አሁንም ሕያው ናቸው። ኢትዮጵያ አገራቸው በጣሊያን ስትወረር ተዋጉ። ጠላትን ካሸነፉ በኋላ የትምህርት ምንስቴር ሆነው በማገልገል ላይ ሳሉ፡- ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ **ፒስኮሮች** ገብተው እንዲያስተምሩ ይፈርሙ ብለው አዘዟቸው። በአካልና በመንፈስ ሊወር የመጣውን ጣሊያንን ታግለን ካባረርን በኋላ፡ ለማላውቀው ሌላ ወራሪ የአገሬን ወጣቶች ጭንቅላትና ስነ ልቡና ይውረር ብየ በመስማማት አልፈርምም አሉ። በዚህ አቋማቸው ከጃንሆይ ጋራ የህሊና ጦርነት ገጠሙ። በዚህ ምክንያት ወደ እንግሊዝ አገር ተላኩ።

እኒህን ኃያል ሰው በመጀመሪያ በአካል ያገኘኋቸው፡ አቡነ ፊልጶስ የኢየሩሳሌም ገዳሙ ጳጳስ በነበሩ ጊዜ የሂብሩና የዓረብኛና የእንግሊዝኛ ቋንቋ አስተርጓሚ ሆኘ ገዳሙን በመገልገል ላይ ሳለሁ፡ ባለቤታቸው ወይዘሮ ከበበ ጸሐይ ኒወርክ አርፈው እሬሳቸውን ኢየሩሳሌም ይዘው መጥተው በሀዘን ላይ በነበሩበት ወቅት ነበር። ሁለተኛ ያገኘኋቸው አዲስ አበባ ነው። አዲስ አበባ ባገኘኋቸው ጊዜ፡ በሥርአቱ ውስጥ እያሉ ፍቅር እስከ መቃብርን ለማዘጋጀት እንዴት ደፈሩ? ብየ ጠየኳቸው። እሳቸውም "የሚያደርገው ሌላ ሰው ከሌለ ለማን ልተወው"? አሉኝ አቡነ መቃርዮስ ቀጠሉና "አየህ !

**"ሰው ማለት**

**ሰው የሆነ ነው፤ ሰው የጠፉ ዕለት"**

የሚባለው ንግግር የሚገልጸው ክቡር አቶ አዲስን ነው" አሉኝ። ስለ አቶ አዲስ ዓለማየሁ አድናቆታቸውን ከገለጹልኝ በኋላ፡ *"ታዲያ ሟቿ ወይዘር ውድነሽ አምሳሉ ከአቶ አዲስ ጋራ በምን ይገናኙ ነበርና ደርበህ አነሳሐቸው?"* አሉኝ።

ደርቤ ያነሳሁበት ምክያት እርሰዎ "ከሳቸው በፊት በሳቸው ዘመንና ከሳቸው በኋላ የተነሱ ጸሐፊወች ለጻፏቸው መጻሕፍት ማእከል ሚዛን ነው" ባሉት መጽሐፋቸው፤ ራሳቸው ክቡር አቶ አዲስ *"ከብዙ ስርዝና ድልዝ ጋራ የጻፍኩትን የመጀመሪያውን ረቂቅ እህቴ ውድነሽ አምሳሉ በብዙ ትጋትና ጥንቃቄ እንደገና ደህና አርጋ ባትጽፍልኝ ኖሮ ብዙ ችግር ይገጥመኝ ስለነበረ ውሊታዋን አልረሳውም"* ብለው በገለጹት በማይረሳው ውለታቸው የወይዘሮ ውድነሽን ማንነት ብገልጽለዎ ለማስታወስ ይቀለወታል ብየ ስለገመትኩ ነው አልኳቸው።

"እንዴ ! እንዴ ! እንዴ ! ክቡር አቶ አዲስ ዓለማየሁ በዚህ አድናቆት ካከበሯቸው፤ እኒህ ሰው ቀደሞ ለአገር ለወገን የማይረሳ ውለታ ከሰሩት፤ አሁንም በመስራት ካሉት፤ ወደፊትም ከሚሰሩት

ኢትዮጵያውያን ሴቶች አንዷ ነበሩ ማለት ነው" ካሉ በኋላ "ትልቅ ኢትዮጵያዊት አርበኛ፤ ጥበበኛና ጸሐፊ ነበሩ ማለት ነው" አሉኝ። ምን ብየ እንድገልጻቸው ይመክሩኛል? ብየ ጠየኳቸው።

"ላንተ ምኑን እነግርሀለሁ። አክብራ ብእሲተ ጠባበ ወኂሪተ እስመ ሞገሳ ይትበደር እምወርቅ። (ሲራክ 7፡19) የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ታውቀው የለም? አሉኝ። ማለትም፡- የሞራል ልዕልናዋ ጥበቧ ትጋቷና ችግር ፈችነቷ ከወርቅ ከዕንቁ ከፍ ያለ ነው። ከዚህ ልዕልና ላይ የደረሰችውን ሴት ከፍ አርገህ አክብራት" እንዲል፡- እነህ እናት የተደነቁበት የክቡር አቶ አዲስ መጽሐፍ ፍቅር እስከመቃብር ለትውልዱ ማስተማሪያ ሆኗል። በኔ ዘመን ያለ ትውልድ አንብቦታል። ወጋየሁ ንጋቱም ሲተርከው ሁሉም ሰምቶታል። አሁንም እየተነበበና ሲተርክ እየተሰማ ነው። ነገር ግን ካንተና በቅርብ ከሚያውቋቸው ሰዎች በቀር ወይዘሮ ውድነሽን ሁሉም ረስቷቸዋል። ወይዘሮ ውድነሽ በአቶ አዲስ የተደነቁ ከሆኑ፡ ቅድም በነገርኩህ መንገድ በዚህ ዘመን ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያት ሴቶች እንዲማሩባቸው አርገህ በመግለጽ አቅርባቸው" አሉኝ።

ወይዘሮ ውድነሽን ለመገለጽ የተሟላ ሀሳብ ፍለጋ ለማግኘት አቶ አዲስ ካዘጋጁት ራሳቸው ወይዘሮ ውድነሽ በቁም ጽሑፋቸው ወደ ጻፉት ወደ ፍቅር እስከመቃብር መጽሐፍ ለመግባት ሽፋኑን ገለጥ አድርጌ ስመለከት፡ *"ከብዙ ስርዝና ድልዝ ጋራ የጻፍኩትን የመጀመሪያውን ረቂቅ እህቴ ውድነሽ አምሳሉ በብዙ ትጋትና ጥንቃቄ እንደገና ደህና አርጋ ባትጽፍልኝ ኖሮ ብዙ ችግር ይገጥመኝ ስለነበረ ውለታዋን አልረሳውም"* የሚለው የክቡር **አቶ አዲስ የምስክርነት ብቅ አለ።**

**ስርዝ ድልዝ** አስተካካይ ብለው ክቡር አቶ አዲስ የወይዘሮ ውድነሽን የስነ ጽሑፍ ጥራት የገለጹባቸው ድርብርብ ቅጽሎች፡- የወይዘሮ ውድነሽን ትጋት ጥንቃቄና ብርታት እያንጸባረቁ ስነባህርያቸውንም ቦግ አርገው አመለከቱኝ። ፍቅር እስከ መቃብር ወይዘሮ ውድነሽን የማይበት ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያን ሁለንተና በምቃኘበት **በግሩም ተራራ** ጫፍ ላይ የወጣሁ መሰለኝ።

"ግሩም ወእቱ ብእሲ ነባቢ በውስተ ሀገሩ ወይጸልእዎ ለዝሉፉ እምነ ቃሉ" (ሲራ 9፡18) ማለትም፡- ባለ ስልጣን ይሸረኛል ይሾመኛል ሳይል የሚጽፍ የሚናገር ሰው በየትውልዱ የሚነገርለት ኃያል ባለ ታሪክ ነው። የሰራው ታሪክ በነጋሪት ድምጽ ታጅቦ የሚሰማበት ተራራ ነው የሚለውን አቶ አዲስ የተገነዘቡ እንደነበሩ ተረዳኋቸው። "ወእምገጹ ለጸሐፊ ይትዐወቅ ጥበቢሁ" (ሲራክ 10፡5) ፡-ማለትም "የጸሐፊን ገጸባህርይ በቤቱ ተደብቆ በሚጽፈው መጽሐፍ ብቻ ማወቅ አይቻልም። በከበቡት ሰወችና በሰራቸው ገጸተባህርያት ነው" እንዲል፡- ትእዛዝ ተቀባይ ብቻ ግዑዝ ያልነበሩትን **ስርዝና ድልዝ** የማይቀበሉትንና ብዙ ችግር ፈች የነበሩትን ውድነሽን ለተወዳጁ መጽሐፋቸው ለፍቅር እስከ መቃብር አርቃቂነት መምረጣቸው አቶ አዲስን ግሩም ሆነው አገኘኋቸው።

<u>የሰው መጥፊያ የሚሰሩትን፤ እስካፍንጫው በታጠቀ ወታደር የተከበቡትን፤ አጥፍተው የሚጠፉን "ኮብላዮች ተቀብዝባዦች" ቃሌላውያን ብሎ እንጅ ፤ መጽሐፈ ቅዳሴያችን ዓለምን ተከትሎ 'ኃያላን" እያለ አያከብራቸውም።</u> "ኃያላን" በማለት የሚገልጻቸው በሰሯቸው ተግባራት በጻፏቸው መጻህፍት፤ በኑሯቸው ገጸተ ባህርያትና የሚገዳደራቸውን መምረጥ ከማይሸሹ እንደ ክቡር አቶ አዲስ የመሳሰሉትን ነው። **"ኃያላን ይጽህፉ ጽድቀ ባቲ"** እንደተባለው አባታችን ክቡር አቶ አዲስ ፍቅር እስከመቃብርን ያረቀቁባት ብዕር የወይዘሮ ውድነሽ፤ የጻፉባት ብራናቸው የወይዘሮ ውድነሽ ጭንቅላት እንደሆነ ተረዳሁ። ከዚህ በመቀጠል በወይዘሮ ውድነሽ ጭንቅላት ላይ በተጻፈው በፍቅር እስከመቃብር ራሳቸውን ወይዘሮ ውድነሽን እንመለከታቸዋለን።

## <u>ሐ. ወይዘሮ ውድነሽ በፍቅር እስከመቃብር</u>

ወይዘሮ ውድነሽን ለዚህ ያበቃቸው የተጠመቁባትን እምነት ተረድተው ከወላጆቻቸው የተማሩት ስርአት እንደሆነ ነግረውኛል። አባታቸው ከሊቃውንቱ አንዱ ነበሩ። ዳዊት ከደገሙ በኋላ ከቁም ጽሑፍ ጋራ የሰሎምንን መጻሕፍት አስተምረዋቸዋል። ካባታቸው ያገኙት እውቀት በአስኳለው ትምህርት ዘልቀው ወደ ዩንቨርሲቲ ሲገቡ መሰረት እንደሆናቸው ይነግሩኝ ነበር። <u>ከተማርኳቸው ትምህርቶች ሁሉ እስከ አለሁባት ቅጽበት አብረውኝ ያሉት አባቴ በጭንቅላቴ ላይ ያስቀመጡት ብራናነቴ እና የጻፉብኝ እኔነቴ (ኢትዮጵያዊነቴ) ናቸው ይሉኝ ነበር።</u>

ወይዘሮ ውድነሽ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን የተፈጸሙትን በጎና ክፉ ስራወች እያነጻጸሩ የወያኔ መንግሥት **የሰረዘውንና የደለዘውን** ኢትዮጵያጵያዊነት አበጥረው እየተመለከቱ እጅግ በጣም ያዝኑ ነበር። ጎራቸውን እየቀያየሩ፡ ራሳቸውን እየለዋወጡ፡ በመንግሥት መድረኮችና አደባባዮች፡ በአብያተ ክርስቲያንም መቅደሶችና አውዶች ላይ ብቅ በሚሉት ሰወች እየተሰቀቁ የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት እነዚህን እንዴት ይገልጿቸዋል? እያሉ ይጠይቁኝ ነበር።

ባንድምታው አመሥጥሯቸው የህብረተ ሰቡን ውጣ ውረድ የሚታዘቡ መምህሮቼ “መንግሥትሰ ትትፋለስ እምህዝብ ሀበህዝብ እንበይነ አመጻ ወእንበይነ ጋእዝ ወእንበይነ ንዋይ ወለምንት እንከ ይትዔበይ መሬት ወሀመድ ዘእንዘ ሕያው ውእቱ ወጽንዕ ነፍስቱ (ሲራ 10፡8 እና 9)። የሚለውን ማለትም፡ “በጭቅጭቅ፡ በንጥቂያ፡ በክርክር፡ በውዝግብ፡ በመሸፋፈጥና በገንዘብ ኃይል መንግሥት ከህዝብ ወደ ህዝብ ይቀያየራል። ያልታሰበ በለስ የገጠመው ተረኛ ይነሳል። በኃይሉ፡ በትእቢቱ ፡እየታገዘ ከህዝብ በዘረፈውና በበዘበዘው ገንዘብ ህዝቡን ሲያስር፡ ሲያሳድድ፡ አየሁህ ! ታዘብኩህ ! ያለውን ሁሉ ያስራል። ይደበድባል። ያሳድዳል። ይገድላል። እሱም በተራው ይፈርሳል። ኃይሉ ሟሙቶ ይጠፋል። የዘረፈው የህዝብ ሀብት ከሳሽና ምስክር ሆኖ ያሳድደዋል። ይህን እያየ ሌላው ተረኛ ይገባበታል። እሱም እንደዚሁ በተመሳሳይ መንገድ ይቀጥላል። ከዚህ አይነት ውዝግብ ያመለጡ *“እህቴ ውድነሽ አምሳሉ በብዙ ትጋትና ጥንቃቄ እንደገና ደህና አርጋ ባትጽፍልኝ ኖሮ ብዙ ችግር ይገጥመኝ ስለነበረ ውሊታዋን አልረሳውም”* <u>ብለው ለርስዎ ምስክር የሰጡት ክቡር አቶ አዲስ ብቻ ናቸው ስላቸው ይደነቁ ነበር።</u>

ወይዘሮ ውድነሽ በተከማቸው እውቀታቸው የቀድሞውን ታሪክ ከዛሬው ታሪክ፤ የቀደመውን ዘመን ከዛሬው ዘመን፤ የቀደመውን ትውልድ ከዘመኑ ትውልድ ጋር በማነጻጸር በፍቅር እስከ መቃብር ይመዝኑት ነበር። እነ ቄስ ሞገሴን የመሳሰሉትን የቀድሞ ዋልጌ ቄሶች፤ በብዙ ድርብርብ ስሞች ራሳቸውን ከጠቀለሉ አስመሳይ ዘመናውያን ቀሳውስት ጋራ ከነፍታውራሪ መሸሻ ጋራ የተሰለፉትን እነ አባ ተክለሃይማኖት የመሳሰሉትን ጆቢራ መነኩሴወች በቁምስና ራሳቸውን ከጠቀለሉ ከተሚዋች ጋራ፡ እንደበዛብህ፡ እንደ ጉዱ ካሣና እንደ አለቃ በላይ የመሳሰሉትን የቀድሞ ፍጹማን ሊቃናት፡ በተናገርነው ከማንገኝ፤ ካፉችን የወጣቸውን ሁሉ ቃል በሳንቲም ድቃቂ ከምንመነዝር፡ ከኔ ቢጤ ጥራዝ ነጠቆች ጋራ እያነጻጸሩ ያዝኑ ይተክዙ ነበር።

በካሳ ዳምጤ ዘመን ይካሄድ የነበረውንና የተናገረውን እየጠቀሱ “ህዝቡን ያስጨንቁ የነበሩትን ሰዎች ካሣ ዳምጤ ሳያፍራቸው ሳይፈራቸው ምን ይላቸው እንደነበረ ታስታውሳለህ ? ይሉኝ ነበር። ካሣ ዳምጤ በዘመኑ ለነበሩት ግፈኞች የተናገረው እንዲህ የሚል ነበር። “የነበረው ስርአተ ማህበር ህይወት እንደ ሌላቸው ድንጋዮች ላይኛው የታችኛውን ተጭኖ፤ የታችኛው የላይኛውን ተሸክሞ እንዲኖር ሆኖ የተሰራ የማይረባ፤ ከጊዜ ብዛት የታችኛው ተሸካሚ ማፈንገጡ ስለማይቀር ህንጻው በሙሉ እንዳይፈርስ እንደገና ተሻሽሎ ሰውን ከተሸካሚ ድንጋይ ለይቶ የሚያሳይ ስርአት መሰራት አለበት። ይህ ስርአት እንዲቀጥል በስብከታቸው እንደ እግዚአብሔር ስርአት አርገው ለህዝብ ይሰብኩት የነበሩትን ሰባኪወች ከብቶች ድንጋዮች“ በዚህ ንግግሩ ካሣ ዳምጤን ፊታራሪወች ጠሉት። በተከታዮቻቸውም አስጠሉት።

ያባቱን ስም ዳምጤን ገፈው ጉዱ የሚል ቅጽል ሰጡትና ጉዱ ካሣ አሉት። <u>አንተስ የዘመኑ ሹማምንትና ጭፍሮቻቸው ጉዱ እንዳይሉህ ይሉቁንም አለቃ፤ መላከ አገሌ፤ ሊቀ ሊቃውንት እንዲሉህ ከነሱ ጋራ ትሰለፋለህ? እነሱን ታወድሳለህ? ወይስ ጉዱ እንዲሉህ ጉዳቸውን ለመግለጽ ትደፍራለህ? በማለት እራሴን በራሴ እንድታዘብ ይረዱኝ ነበር።</u>

የኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስደት ሲሰሙ ያባቶቻቸውን ሀዘንና ትካዜ የአቶ ቦግአለ ሙብራቱን ሀዘንና ትካዜ እያስታወሳቸው፤ ልጃቸው በዛብህ ጠፍቶባቸው *“መነሻውና መድረሻው በማይታወቀው የሀሳብ ባህር ጠልቀው፤ ያለፈው የህይወት ታሪካቸውና የሚመጣው አንድ ላይ ተጠራቅሞ ተደባልቆ የፈጠረው ጥልቅና የሀሳብ ማዕበልና ሞገድ ኢያላጋቸው ራሳቸውን ኢያወዛወዙ ዓይኖቻቸውን ለበስ አርገው ለምን ሚስት አገባሁ? ለምን ልጅ ወለድኩ? ከድሮው ኑሮየ ምን ቀለለልኝ። ምንስ ተሻለኝ ባሰብኝ እንጅ”* (ም 2 ገጽ 22) እያሉ እንዳነቡት ዛሬም ኢትዮጵያውያን አባቶች እንደ አቶ ቦጋለ ስለጠፉት ልጆቻቸው ማንባታቸውን እንደቀጠሉ ታያቸዋለህ? ያውም ከቀድሙ አባቶች እጅግ በባሰና በከፋ ሁኔታ! ይሉኝ ነበር።

የበዛብህ እናት ከጥጋቸው ጠፍቶባቸው *“ወልጄ አሳድጌ በመጦሪያየ ጊዜ ልጄን አስኮብልሎ እኔ አገር ጥየ ስሄድ ለካዳካማዋ እናቴ ማን አላት እንዳይል ልቡን አደንድኖ አዕምሮውን ሸፍኖ ልጄን እንዲኮበልል ኢደረገው ይህም አልበቃ ብሎ ዓይኔን አሳወረኝ ከዚህ የባሰ ምን ይመጣብኛል ? ሞት ነው። ባንድ ፊቱ መሞት ይሻለኛል” (ፍ. እስከ ምዕ 5፡ ገጽ 48)* እያሉ ያለቀሱትን ልቅሶ ከዛሬይቱ ኢትዮጵያዊት እናት ልቅሶ ጋራ ያነጻጽሩት ነበር። የዛሪይቱ ኢትዮጵያዊት እናት እየተማረ አድጎ ለአገር ለወገን መከታ ይሆናል ለኔም ትሩፋቱ ይደርሰኛል ብላ ቅጠል እየሸጠቺ ያስተማራችው ልጇ ከጉያዋ እየታነቀ በመንግስት ከፊቷ ላይ ሲገደል፤ ሌላው ሞት ሸሽቶ በተሰደደበት አገር በሰይፍ ሲታረድ እያየች የምታነባው እንባ፤ ከበዛብህ እናት እንባ እጅግ የከፋ እንደሆነ ወይዘሮ ውድነሽ እያሰቡ ምርር ብለው ያለቅሱ ነበር።

“የጎሳ መሪወች ነን እያሉ ከየጎጡ፡ መንፈሳውያን አባቶች ነን እያሉ ከየደብሩ የሚፈሉት፡- የኑሮው ውጣ ውረድ የሚያላጋው አንሶት የወለደውን ልጁን እየደበደቡ እንደ እስስት እያነቁ ግፈኞች ሲገሉበት ቆመው እያዩ፡- በዝሙቱ፡ በሙብሉናበመጠጡ ላይ ብቻ ተሰማሩ። ተልእኳቸውን በመዘንጋት በግል ጥቅማቸው ላይ ብቻ አተኮሩ። በህዝብ ላይ ተደራርቦ የሚፈጸመውን ግፍና በደል በይሉኝታና በፍራቻ ወይም በግል ጥቅም ተደልለው ቆመው ማየት የቀፈፋቸው **የዲማው አለቃ በላይ** “ሰው አራት እግር ካላቸው እንስሳት የሚለየው በሁለት እግር ቆሞ መታየቱ ነው። ልዩነቱ በሁለት እግር ቆሞ መታየቱ ከሆነ ዶሮም ሁለት እግር አላት። ሰው ከሁሉም የሚለየው ራሱን መግታት መቻሉና ራሱን የሚገዛ ትውልድ ተክቶ ማለፉ ነው” ይሉ ነበር (ፍቅር እስከ መቃብር ምራፍ 2 ገጽ 24) ። <u>አንተን የተኩህ መምህሮችህ ሁለት እግር ያላቸው ዶሮወች ነበሩ? ወይስ ራሳቸውን መግታት የቻሉ፡ አንተንም እንደራሳቸው ራሳህን መግታት እንድትችል ቀርጸውና አስተካክለው የተኩህ ነህ? ይሉኝ ነበር።</u>

የናታችን ውድነሽ እነዚህ የመሳሰሉት ፈታኝ ጥያቄወቻቸው የቀድሞ ሊቃውንት ዘመናቸውንና ትውልዱን እየታዘቡ ሲገስጹባቸው ወደነበሩት ጥልቀታቸውን ወደማልወጣው ቅኔወቻቸው ገፍትሮ ይከተተኝ ነበር። ከብዙወቹ ቅኔወች አንዱ በ1880 ዎቹ አካባቢ በነ ራሲ አሊ ዘመን የነበሩት የመጋቢ መርሻ ኃይሉ ቅኔ ነው ። መጋቢ መርሻ ኃይሉ፡- ህዝባቸው በሹመኞቹ ከሰውነት ወጥቶ ወደሚጎተት እንስሳነት መግባቱን ተመልክተው በዚህ ቅኔያቸው እንዲህ እያሉ ገልጸውት ነበር።

*“መኑ የአምር ዕለተ ሥቃዩ፡- ወመኑ የአምር ዘይመጽእ መከራሁ፤*

እስመ ሕሊና ሰብእ ኮነ ሕሊና እንስሳት ዘበዝኍ፤
ምሳሌ ዝኒ ከመ ናእምር፡- ቃየል እመ ተበቀሎ ለአቤል እኍሁ”
እንዘ አቤል ቤተ ሙሴ፡- ኢያእመረ አቤል  ምክረ ቃኤል ቀታሊሁ፤
አዳምኒ እንዘ በኩሉ በዐለ አዕምሮ ለሊሁ፤
አዳም ኢያምሰጠ እመስገርተ ቤልሆር ጸላኢሁ፤
ወለእመ ነሐትት    ንህነ አምላከ አማልክት ኪያሁ፤
ጠቢብ ወማእምር አልቦ ዘእንበሌሁ”

ግእዙ የተሸከመውን የቅኔውን ለዛና ውበት በዚህች አጭር አገላለጽ ይገለጻል ባልልም፤ ቅኔው የተዋቀረበት   ምሰሶ የሚከተለው ነው። ባለ አዕምሮው አዳም በሰይጣን የተዘረጋለትን ማስተዋል አቅቶት በወጥመድ ወደቀ። ልጁ አቤልም በወንድሙ ቃኤል የተጠመደለትን የሞት ወጥመድ መረዳት ተስኖት ተጎትቶ በሞት ጉድጓድ ገባ። ሁሉም ገዳያቸው በፊታቸው የዘረጋላቸውን ወጥመድ ባለማስተዋላቸው ከእንስሳት አልተሻሉም“ የሚል ነው። ይህ ከዛሬ 150 ዓመት በፊት መጋቢ መርሻ ኃይሉ የተቀኙት ቅኔ፤ አዳም በሰይጣን የተዘረጋለትን ማስተዋል አቅቶት በወጥመድ እንደወደቀና።  አቤልም በወንድሙ ቃኤል የተጠመደለትን የሞት ወጥመድ መረዳት ተስኖት ተጎትቶ በሞት ጉድጓድ እንደገባ ያሳስባል።

እኔም በእጸበለስ ተጎትቶ ወደ ወጥመድ እንደገባው  አዳም፤በዘመኑ እጸ በለስ ተጎትቼ ወደጥፋት እንዳልገባ የ**አለቃ በላይን**  ሐዋርያዊ  ተግሳጽ እያነሱ በሚጠቁሙኝ  ቀስቃሽ ምክራቸው የነመጋቢ መርሻ ኃይሉን ቅኔ ሁሉ እያስታወስኩ  እንድጠነቀቅ ወይዘሮ ውድነሽ ምክንያቴ ነበሩ።

ከወይዘሮ ውድነሽ ጋር በስልክም በአካልም ስንገናኝ፡- ከህዝቡ ጎን ቆመው መንግሥት ታራሚወች ሽፍቶች እያለ የሚያወርድባቸውን ዘለፋ እስራትና ግርፋት ተቋቁመው የሚፋለሙትን በፍቅር እስከ መቃብር በተገለጸው በአበጀ በለው ሥነ ልቡና እያየን እናደንቃቸው ነበር።

በዚያ ዘመን በነ አበጀ በለው ገጸ ባህርይ የተገለጹ  የጎበዝ አለቆችና ፋኖዎች ነበሩ። በዚያ ዘመን የነበሩ ፍታውራሪወች፤ ሽፍቶች ፤ ወንበዴወች  የሚል ቅጽል  በመስጠት ከህዝብ መካከል እየለዩ የጊዜው ሹማምንት ያስድዷቸው እንደነበር። በዘመናችንም ህዝብ በማስጨነቅ ላይ ያሉትንና፤ የህዝቡን ጭንቀት ለማስወገድ የሚታገሉትን የጎበዝ አለቆችንና ፋኖወችን፤ ታራሚወችና ሽፍቶች እያሉ ከድሮው አሳዳጆች እጅግ የከፉ አሳዳጆች የሚፈጽሙባቸውን ማሳደድና መግደል እየተመለከቱ፤ በዚያ ዘመን ካሳዳጆች ጋራ እየበሉ እየጠጡ ደበሏቸውን እስኪጥሉ ድረስ ሰክረው የሚዘላብዱት እነ አባ ተክለ ሃይማኖትን ልክ አይደላችሁም ተሳስታቿኋል ያሏቸውን  “ጉዱ ካሣ” እያሉ እነ ካሣ ዳምጤን ያሳድዱ እንደነበር፤ የዛሬወቹ አባወችም ልክ አይደላችሁም ተስተካከሉ የሚሏቸውን፤ የቀድሞወቹ ከፈጸሙት ማሳደድና ስም ማጥፋት የከፋ ስደትና ዘመቻ የዛሬወቹ የሚፈጽሙትን እያዩ እጅግ በጣም ያዝኑ ነበር።

_“ሥልጣን  በዙሪያቸው አጥረው በሥልጣን ተሸሽገው  ድሀ የሚዘርፉትን እቃወም ነበር እንጅ ሽፍታም ቀማኛም አልነበርኩም። እቤቴ ተቀምጬ ቀማኞች ባለ ሥልጣናት በህዝብ ላይ የሚሰሩትን ግፍና በደል እያየሁ መቃወም ባለመቻሌ ቤቴን ትቼ መሰደዴ ሽፍታ አያሰኘኝም። የድሀ ህይወትና ንብረት የሚጠበቅበት የተሰራና የተሰጠ ህግ ተጣሞና ተቆልምሞ የድሀ ህይወት ማጥፊያን ንብረት መዝረፊያ ለአመጽ ማስፈጸሚያ ሲሆን ማየት ይቀፈኛል። ያንገፈግፈኛል እንጅ ሽፍታ አይደለሁም” እያለ በዘመኑ የነበሩትን ሽፍጠኞች ይፋለማቸው የነበረውን አበጀ በለውን፤ እኛ ነፍጠኞች አርበኞና አራሚወች እንጅ፤ እንደናተ ነውረኞች፤ ሽፍጠኞች ነውጠኞችና  ታራሚወች አይደለንም  እያሉ በመታገል ላይ ካሉት ጋራ እያነጻጸሩ ወይዘሮ ውድነሽ ይገረሙ ነበር። “አንተ እንደነሱ መሆን ባትችል እንኳ ፡ ልትቀኝላቸው አትችልም” ይሉኝ ነበር። “አዬ እናታችን ቅኔ በውስጠ ወይራ፤ በውስጠዘ በመሳሰሉ ቀመሮች በዘመኑ

የሚታዩትን ፈትሎና  እንደቀይ ሽንኩርት ደራርቦ የሚዘጋጅ ነው። ቅኔ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለት አድማጭ የተደራረበውን እየላጠና እየፈለቀቅ የማየት አቅም ሊኖረው ይገባል። ይህን ማድረግ የሚችለው በሙያው የለፋና ያልሞተ ስሜት ያለው ነው። በዚህ መንገድ የሚዘጋጀውን ቅኔውን ልተወውና ያዘዙኝን ለመፈጸም ያልጠፋውን የጎንቻው የአበጀ በለውን  ስሜት በነ እስክንድር መታየቱን የሚገልጽ ግጥም ልሞክርልዎ ብየ፡-

“በጎንቻ ጧፍ ሆኖ የነደደው ሰም
በነፈሰው ነፋስ ሊጠፋ አልቻለም
በአበጀ በለው እጅ አላለቀም ቀልጦ
ለነ እስክንድር በራ ታስረው በቅሊንጦ። ”

የምትል ግጥም አሰማኋቸውና ደስ አላቸው። ”እንደ መምህሮችህ ጋን መሆን ባትችልም ምንቸት ሆነሀል” ብለው ቀለዱብኝ። ወይዘሮ ውድነሽ  “እስቲ ያሳይህ ! እነ ፍታውራሪ መሸሻ አበጀ በለውን ሽፍታ ያደረጉበት ምክንያት ምንድነው?እነ ቄስ ሞገሴ ከነ ፊታውራሪ ጋራ ተባብረው አበጀ በለውን ሽፍታ የሚሉት እንደነሱ የቄስ ልብስ አለመልበሱ ብቻ አበጀ በለውን  ሽፍታ ያደርገዋል? የሽፍታ ስራ እየሰሩ የቄስና የመነኩሴ ልብስ  ለብሰው ሰውን እሁድ እሁድ ንስሀ ግቡ እያሉ ማደንቆራቸው ብቻ፡ እነ ቄስ ሞገሴንና እነ አባ ተክለ ሃይማኖትን የክርስቶስ ተከታዮች ያደርጋቸዋል? ብላችሁ ታስባላችሁ? ይሉኝ ነበር።

ወይዘሮ ውድነሽ የጠቀሱት አበጀ በለው መታለፍ የሌለበት ከራሱ  ጋራ የተያያዘ የማያልፉት ትውስታ ነበራቸው። ግፈኞችን ከጥፋታቸው እንዲገቱ፡ ባይገቱና በጥፋታቸው ርቀው ቢሄዱ፡ የህዝቡ ብሶት ማእበል ሆኖ እንደሚያሰምጣቸው ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ግጥም የጎንቻ ሳር ምድር ህዝብ ለግፈኞች  እንዲያደርስሰለት በጨርቅ እራፊ ቋጥሮ የሰጠውን የግጥም ጽሑፍ፤ አበጀ በለው ለግፈኞቹ በማድረስ ብቻ ሳይወሰን፡ በሥራ ለመተርጎም ያደረገውን ጥረት ሳያስታውሱ አያልፉትም ነበር። ግጥሙም ይህ ነበር።

“አንበሳ አረጀና እቤት በመዋሉ
አራዊት ተጨንቀው የት ደረሰ እያሉ
ነብር ተነሳና ከመካከላቸው
እኔ ነኝ አንበሳ እጅ ንሱኝ አላቸው
ነብር ነብር እንጅ አንበሳ እንዳልሆነ
ምንም የታወቀ ቢሆን የታመነ
ደፍረው ሊናገሩት ሁሉም ስለፈሩ
ለነብር ማደግደግ እጅ መንሳት ጀመሩ
ሌሎች እንዲፈሩት እንዲሰግዱለት
አንበሳ ነኝ ብሎ በዋሸው ውሸት
አመነበትና ከጊዜ ብዛት
እሱም ማን መሆኑን ጀመረ መርሳት
አንበሳ ነኝ ብሎ ተቀመጠ ቤቱ
ሌሎችም ነህ ብለው ሲሰግዱ ከፊቱ
አንበሳ መኖሩን ገና በህይወቱ
በሩቁ ሲወራ ድንገት በመስማቱ
ሁሉም አምኖ እንዲኖር ነብር ያለውን

ከሱ ሌላ አንበሳ አለመኖሩን
አዋጅ አዋጅ ብሎ ሰብስቦ ዓለሙን
አንበሳን ሰደበ ከፍ አርጎ ድምጹን
የተኛው አንበሳ እድሜ ተጭኖት
የነብርን ስድብ ሰማና ድንገት
አጉራርቶ ቢነሳ ወኔው ቀስቅሶት
ነብር ግራ ገባው መሄጃ ጠፋው
መሬት አፏን ከፍታ ድንገት አትውጠው
ሰማይ እንዳይወጣ ክንፍ አልነበረው" (ፍቅር እስከ መቃብር)

ይህ የጎንቻ ህዝብ ግጥም በሕዝቡ ስሜት ውስጥ አንቀላፍቶና ተዳፍኖ ሲኖር በአቶ ወጋየሁ ንጋቱ ውርድ ንባብ የተነበበው እንደገና በኛ ዘመን በነቴዲ አፍሮ የቀረበው ዝማሬና ቅላጼ በጎንደር፡ በአዲስ አበባና በባህርዳር ኢትዮጵያውያንን ያዘፈነው ዘፈን፡ ያዘመረው ዝማሬና ያሰረገደው መረግድ፡ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ የነጻነት ደመና ሰፎበት እንዳይ አድርጎኛል" ይሉ ነበር።

የነቴዲ ቅላጼ፡ የነ ሽመልስ ለገሰ ያላሰለሰ እንቅስቃሴና የኃያላን ጸሐፍት ተናዳፊ ብእር ተባብረው በሚያካሂዱት ቅስቀሳ፡"ወያኔወች በኢትዮጵያና በርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ በየእለቱ እያበዙትና እያከበዱት የሚጭኑትን መከራ መሸከም የከበደው ህዝብ፤ አሽቀንጥሮ በቅርቡ ሲወረውረው ሳላይ አምላኬ እንደማይገለኝ አምናለሁ" ይሉ ነበር።

"እኔን በእጅጉ የሚያሳስበኝና የሚያስጨንቀኝ ቅዱስ ጳውሎስ "የቀረውን ነገር ሳልቆጥር በየዕለቱና ሰአቱ የሚከብደኝ የአብያተ ክርስቲያናት አሳብ ነው"(2 ቆሮ ፲፩፡ 28) እንዳለው፤ በዚህ ዘመን እንደ ጉዱ ካሣ እንደ አለቃ በላይ የመሳሰሉ ሊቃውንቷን ትቀርጽበት በነበረው ስልቷ ቀርጻ ያፈራቻቸው መንፈሳውያን ሊቃውንት ባሁኑ ጊዜ የሌላት የቤተ ክርስቲያናች ነገር ነው ይሉ ነበር። ዶ/ር ዓቢይ ወደ አሜሪካ መጥተው የተለያዩትን ሲኖዶሶች አስታርቀው ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስን ወደ ኢትዮጵያ ይዘው ለመሄድ ያቀረቡት ሀሳብ ያስነሳውን ውዝግብ ወይዘሮ ውድነሽ ሰምተው የተናገሩትን አስደናቂ ነገር ከዚህ ቀጥየ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## ረ. ወይዘሮ ውድነሽ በዶ/ር ዓቢይ ፊቃጅነት በተፈጸመው የሲኖዶሱ እርቅ

ዶክተር ዓቢይ ወደ አሜሪካ መጥተው ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከሳቸው ጋራ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተዘጋጅተው እንዲቆዩዋቸው ወደ ሎሳንጀለስ ሄደው በቆዩባቸው እለታት፡ ይመለከተኛል የሚለው ሁሉ Hampton in Hotel 501 New York Ave Ne Washington Dc 20002 በሚባለው ሆቴል እየተሰበሰበ "ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከዶ/ር ዓቢይ ጋራ አብረው ወደ ኢትዮጵያ ይሂዱ? ወይስ አይሂዱ?" የሚለውን ሀሳብ መነጋገሪያ አደረገው።

አቡነ መርቆርዮስን ጠቅላይ ምንስቴሩ እግረ መንገዳቸውን ይዘዋቸው ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገቡ ወሬው ደርቶ በይፋ ሲወራ በሰሙ ጊዜ፡- ወይዘሮ ውድነሽ በእርቁ መጀመር እጅግ ቢደሰቱም ከእርቁ በኋላስ ምን ይከሰት ይሆን? እያሉ ይጨነቁ ነበር። በአስታራቂነት በተሰለፉ ሰዎች መካከል በየዋህነት የገቡ ቢኖሩም፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚያንዣብበውን የታሪክ ጠለሸት ርቀው መመልከት የማይችሉ ሰዎች የበዙበት እንደነበረ ከሚናገሩት አስተዋዮች አንዷ ነበሩ።

"ብጹዓን ቅዱሳን የምንላቸው አባቶቻችን፡እስካሁን በዓለምና በመላ ኢትዮጵያውያን የሚታወቁት እርስበርሳቸው ተጣልተውና ተኳርፈው የጸብና የኩርፊያ አገልጋዮች ሆነው ነው። ጸብን እያወገዙ

የተጣላውን እያስታረቁ የተሰየሙለትን የማስታረቅ ተልእኮ ከሚጣላውና ከሚያጣላው ፖለቲካ በታች እንዲወድቅ ማድረጋቸው አንገታችንን እንድንደፋ አድርገውናል። አዲሱ ፖለቲከኛ ዶ/ር ዓቢይ የሚባለው ታረቁ ማለቱ መልካም ነው። የፖለቲካ ስራውን እነሱን በማስታረቅ መጀመሩም የተቀደሰ ነው።

"ኢትዮጵያ የሚባለውን ስም ጠልተው ሲያስጠሉ፡ ቤተ ክርስቲያንን ከፍለው ሲያከፋፍሉ የቆዩት ፖለቲከኞች በአካል ተወግደው፤ ኦርቶዶክስን ከአማራው ጋራ ሰበርነው የሚለው ፉከራቸው ከስሞ ፤ እናት አገራችን ኢትዮጵያ እያለ፤ ታሪካዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችንን አገር ናት እያለ ሲመጣ እንደታምር በመቁጠር ዶክተር ዓቢይን የማይደግፈው የለም። በዚህ አመጣጡ ብንደግፈውም ያደገበት ያመነበትና የሚከተለው ፖለቲካ በሚያስከትሉት ተጽእኖ አሁን የሚታዩት ሁለንተናወች እንዳሉ አይቀጥሉም። በፖለቲከኛ የሚጀመር ነገር ሁሉ የሚያልቀው በራሱ ፖለቲካ መሆኑን የቤተ ክርስቲያኒቱ ካህናትና ምእመናን መዘንጋት የለብንም። ሰውየው ከመልካም ህሊና ቢያደርገውም ፖለቲከኛ ነውና ውሎ አድሮ መመጻደቂያ ለማድረግ መፈተኑ አይቀርም። ወደፖለቲካው ውስጥ እየሰመጠ ሲገባ፤ ለሚወዱት ለሚከተሉት ለሚደግፉት የነካው የዳሰሰው የተናገረውና የተነፈሰው ሁሉ ፈውስ መድህኒት የሚያረጋጋ የሚያዝናና እየሆነ፤ ለሚቃወሙትና ለሚቀናቀኑት ጢስና በርበሬ እየሆነ ማስጮሁ ማስነጠሱና ማስለቀሱ የሚቀር አይደለም። ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ በሱ ታዝለው መግባታቸው ለጊዜው መልካም ቢመስልም፤ ውሎ አድሮ ለአባቶችም፤ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለራሱ ለፖለቲከኛውም እንኳ ቢሆን የሚበጅ አይመስለኝም።

በተቃዋሚወች ዓይን ላይ የሚበትነውን አፈርና ገለባ ማግበስበስ ሲጀምር ለመጀመሪያ አፍሶ መበተን የሚጀምረው፤ ያደረኩላችሁን ሌላውን ሁሉ ብትረሱትም የሃይማኖታችሁ መሪወች ብጹአን ቅዱሳን የምትሏቸውን ሰዎች ያስታረኩላችሁ እኔ አይደለሁም ! እናንተ ናችሁ ! ማለቱ አይቀርም። የሱ ፖለቲካ ደጋፊወች፤ የፖሊሲው አራማጆችና የሃይማኖት ማህበርተኞቹ ብጹዓንና ቅዱሳን የምትሏቸው መሪወቻችሁ መታረቅም ማስታረቅ የማይችሉ ደካሞች በመሆናቸው የኛ ፖለቲካ መሪያችን፡ የኛ ሃይማኖት ተከታያችን አይደለም እንዴ ! ያስተረቀላችሁ ! ማለታቸው አይቀርም። በሚቀናቀነው ላይ ለካ ለፖለቲካው ማዳበሪያና ማዳመቂያ ለማድረግ ነው በሚል በራሱ ላይ የፖለቲካ ትዝብት ይፈጥርበታል። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩም ይህን ሲሰማ፡ አሰዳቢወችና አዋራጆች የሚል ትዝብትና ጥላቻ በሁለቱም ፓትርያርኮች ላይ ያሳድራል" አሉኝ ። ታዲያ ምን ማድረግ ይሻላል ? አልኳቸው።

ያጣላቸው መንግስት ነው ሲባል ነበር። አሁን መንግስት ታረቁ ካለ፡ ሁለቱ ፓትርያርኮች በያሉበት ዝም ብለው የተቀመጡት ምን እየጠበቁ ናቸው ? ሁለቱም ፓትርያርኮች ከየተቀመጡበት ተነስተው፡ ድሮም ያጣላን መንግስት እንጅ በመካከላችን ከሰላም ከብጽዕና ከቅድስና በቀር እንኳን አኮራርፎና አቀራርጦ ይህን ያህል ዘመን የሚያቆይ ጸብ፤ ወቅታዊት የቃል ግጭት በመካከላችን አልነበረብንም ተባብለው እርቁን ራሳቸው ፈጥነው መፈጸም ይገባቸዋል። ተበደልኩ ተገፋሁ የሚሉትን አቡነ መርቆርዮስን፤ አቡነ ማትያስ ብድግ ብለው መተው፡- ወንድሜ ባስቀየምኩዎ ይቅርታ ይነሱና እንሂድ፤ ወያኔወች የሰበሯትን ቤተ ክርስቲያናችንን አብረን እንጠግናት። ከቤተ ክርስቲያናችን ጋራ አብሮ የተሰበረውንና በብዙ መንገድ የተዘመተበትን አማራውን በየደብሩ፡ በመንደሩ እየዞርን ይቅር በለን እያልን ተሰብሮ ከወደቀበት እናንሳው፤ ከተበተነበትም እንሰብስበው ብለው ራሳቸው ካስታራቂወች ሽማግሎች ጋር ሆነው ይዘዋቸው ቢመለሱ የሚበጅ ይመስለኛል" አሉ ።

በመቀጠልም "ይህን እንዲያደርጉ መርዳት የነበራችሁ በዙሪያቸው ያላችሁ እናንተ የዘመናችን ካህናት ነበራችሁ። የህብረተሰቡን ቀልብ ወደራሳችሁ እየሳባችሁ ማንነታችሁን ለይቶ ማወቅ የማይችለውን ህዝብ አላቢውን ቆሞ እንደሚጠብቅ የላም መንጋ እናንተ ባጠራችሁለት በረት እየከተታችሁ ቆሞ እንዲታለብ በማፍዘዝ ላይ ናችሁ። ግማሾቻችሁ ራሳችሁን እንደ ባእድ አድርጋችሁ ቆማችሁ

በመታዘብ ላይ ናቸሁ። ከዚህ ሁሉ ደካማ አስተሳሰብ ተላቃችሁ እንደ ጉዱ ካሣ ቤተ ክርስቲያችን በጻፈችው መንገድ ብቻ ችግሩን ለመፍታት የምትታገሉ በእውነተኞች ሊቃውንት ጉባዔ የተቀርጻችሁ ብትሆኑ ኖሮ ለፖለቲካውም ለቤተ ክርስቲያንም የሚበጅ ትልቅ ስራ በሰራችሁ ነበር“ አሉ።

ለቤተ ክርስቲያንም የሚበጀው የሚሰራው ስራ ምን ይመስለወታል? ብየ ጠየኳቸው። ” ቅድም የነገርኩህን ሁለቱም ፓትርያርኮች ከፖለቲካው ቀድመው እንዲያደርጉ መምከር ነዋ ! ” አሉ። ቀጠሉና “አንተስ ብትሆን የማንን ጎፈሪ ታበጥራለህ? ከጥቂት አመታት በፊት ይመስለኛል ዲሲ መጥተህ ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ቀድሰው ሲያቆርቡ አብረህ ቀድሰህ ቆርበሀል። አቡነ መልከ ጼዴቅም እየጋበዙህ በስብሰባቸው በመገኘትህ የውጩ ሲኖዶስ ደጋፊነትህ የታወቀ ነው። ከፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ጋርም በመታረቅ የቀድሞ ፍቅራችሁ ተመልሷል። ለሁለቱም ይህን ሀሳብ ለምን አታቀርብላቸውም ?” አሉ።

በበነጋው የዲስ ግብረ ኃይሎች አቡነ መልከ ጼዴቅ ከኦክላንድ መምጣታቸውን ሰምተው “ልናገኛቸው እንፈልጋለንና አንተም ከኛ ጋራ አብረን ልናገኛቸው ፈልገን ነበር” ብለው ካለሁበት ቦታ መጥተው ወደ ሆቴል አብረን ሄድን። አቡነ መልከ ጼዴቅ ያረፉበትን ክፍል ስንፈልግ፤ ዶ/ር አምባቸው ወሮታ አቡነ መልከ ጼዴቅ የሚያርፉበትን የመኝታ ቤት ቁልፍ ይዘው ከፕሮፌሰር ይሳቅ ጋር የወቅቱን ነገር እያወጉ ሲጠብቋቸው አገኘናቸው። ከነፕሮፌሰር ይሳቅና ከዶ/ር አምባቸው ጋራ ሰላምታ ተለዋውጠን ስለወቅቱ ጉዳይ ጥቂት ካወጋን በኋላ፤ ከተለያየ አገር መጥቶ በሆቴሉ ያረፈው ሰው እርስ በርሱ ሰላምታ እየተለዋወጠ የወቅቱን ነገር ይወያያል። ካስታራቂወች አንዱ መላከ ገነት ገዝሀኝ እኔ ከነበርኩበት ትንሽ ራቅ ብሎ ከሚወያይ ቡድን ጋራ ነበሩ። እርስ በርሳችን በሩቅ ተያየንና እሳቸውም ወደኔ ሲመጡ፡ እኔም ወደ እሳቸው ስሄድ በመካከል ተቀምጦ ከሚወያየው ቡድን ላይ ተገናኘንና ሰላምታ ከተቀያየርን በኋላ ቡድኑን ተቀላቀልን።

ከተቀላቀልነው ቡድን ውስጥ ከነበሩት አንዱ የስያትሉ አቡነ ማርቆስ “የፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ከዶ/ር ዓብይ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ መሄዳቸውን እንዴት ይመለከቱታል ? ብለው ጠየቁኝ። ከወይዘሮ ውድነሽ የሰማሁት ትዝ አለኝና “ከዶ/ ር ዓቢይ ጋራ ባይሄዱ ይሻላል” አልኩ። ይሻላል ያልኩበትን ምክንያት ሳይረዳ ፤ “ባይሄዱ ይሻላል” ያልኳትን ሐረግ ብቻ የሰማ በጥጋችን የነበረ ሰው “እንዴት አይሂዱ ትላለህ? ብሎ በቁጣ ቃል የገላመጠን አልረሳውም። ማታ ከወይዘሮ ውድነሽ ጋራ በስልክ ተነጋገርን። ሕዝቡ “ይሂዱ አይሂዱ” እየተባባለ የሚወያየውን አካፈልኳቸው። “ራስህ ጉዱ ካሳን ለመሆን ለምን አትሞክርም?”አሉኝ። እንዴት አድርጌ?አልኳቸው። ”የነገርኩህን ለፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስ ነገራቸው። ለፓትርያርክ አቡነ ማትያስም ደውለህ አካፍላቸዋ ! ” አሉኝ። በአሁኗ ጊዜ ፓትርያርክ አቡነ መርቆርዮስን የከበባቸው ብዙ ነው። ባገኛቸውም እርሰወ የነገሩኝን ሀሳብ ብናገር በዙሪያቸው የከበባቸው ህዝብ በተለያየ ስሜት ተውጧልና አንጃ ከመፈጠር በቀር ውጤት አይኖረውም አልኳቸውም። አይሆንም እንጅ ከሆነ የሚቀለኝን ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን ማነጋገር ነው አልኳቸው።

የዚያኑ ማታ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስንና እኔን አቀራርቦ ባስታረቀን ወዳጃችን አማካይነት ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን በስልክ አግኝተን ከወይዘሮ ውድነሽ የሰማሁትን አካፈልኳቸው። ፓትርያርክ አቡነ ማትያስም “መልካም ሀሳብ ነው ለማድረግ እሞክራለሁ” አሉኝ። አቡነ ማትያስን አግኝቼ መንገሬንና እንደተስማሙብትም ለወይዘሮ ውድነሽ አካፈልኳቸው። ወይዘሮ ውድነሽም “ያድርጉት አያድርጉት የራሳቸው ሀላፊነት ነው። አንተ ግን ሀላፊነትህን ተወተሀል። አሁን ጉዱ ካሳ መሆንህን አየህ ተረዳህ አደል ? ” አሉኝ። ከሳምንት በኋላ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን ደውለን ጉዳዩ እምን እንዳደረሰ ጠየኳቸው።

“ባካባቢየ ካሉት ጋራ ሀሳቡን ተካፈልኩት ፡፡ ያካፈልኳቸው ሰወች ሀሳቡ ቀደም ብሎ ቢደርሰን መልካም ሀሳብ ነበር፤ አሁን ግን በዶ/ር ዓቢይ አመራር በተቃኙ ሰዎች እጅ ላይ ስለወደቀ፡ ብቻየን ላደርገው አልቻልኩም” የሚል መልስ ሰጡን፡፡ አቡነ ማትያስ የነገሩኝ አንስተን ከወይዘሮ ውድነሽ ጋራ ተነጋገርን፡፡ ወይዘሮ ውድነሽ ስርዝ ድልዝ እያስተካከሉ የፍቅር እስከ መቃብርን ረቂቅ በሚጽፉበት ጊዜ፡ በጭንቅላታቸው ተቀረጾ የቀረ ተመሳሳይ ነገር ትዝ ብሏቸው ጠቀሱት ፡፡

ወይዘሮ ውድነሽን ትዝ ያላቸው፡ **እነ** ፍታውራሪ መሸሻና ፍታውራሪ አሰጌ የሚሰሩትን ስህተት ከማቃናት ይልቅ፤ በጥፋታቸው ይተባበሩ ስለነበሩት ስለነ ቄስ ሞገሴ፡ ጉዱ ካሳ የተናገረው ነበር፡፡ የጉዱ ካሳ **ንግግር “ የራሳቸው ሀሳብ የሌላቸው የሰውን ሀሳብ ብቻ ከዓይን ከግንባር እያነበቡ አይተው የሚተረጉሙ ሆዳቸውን እየሞላ የሚመራቸውን የሚከተሉ ክህነታቸውንና ተግባራቸውን ለሆዳቸው የሸጡ የለወጡ ናቸው”** የሚል ነበር፡፡ ሁለታችንም “አየ አለመታደል እነ ቄስ ሞገሴን በመሳሰሉ ሰዎች ተከበዋል ማለት ነው” ተባባልን፡፡ “እኔም፡- ሊቃውንቱን እያሳደዱ በዙሪቸው የከበቧቸውን እነ አባ ሞገሴን በቤተ ክርስቲያችን ሀብት ከማበልጸግ በቀር፡ ለቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለህዝበ ክርስቲያኑ እስካሁ የሰሩት የለም፡፡ ከእንግዲህም የሚሰሩት አንዳች ነገር እንደማይኖር ተረዳሁ” አልኳቸው፡፡

እንዲያውም ከታረቁ በኋላ ችግሩ እየዋለ እያደረ ከቀድሞው እጅግ እየከፋ ሄደ፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ፡፡ ምእመናን በየቦታው በሜንጫ ታረዱ፡፡ ወጣት ልጃገረዶች ታፈኑ፡፡ “መነሻውና መድረሻው በማይታወቀው የሀሳብ ባህር ጠልቀው፤ ያለፈው የህይወት ታሪካቸውና የሚመጣው አንድ ላይ ተጠራቅሞ ተደባልቆ የፈጠረው ጥልቅና የሀሳብ ማዕበልና ሞገድ እያላጋቸው ራሳቸውን እያወዛወዙ ዓይኖቻቸውን ለበስ አርገው ለምን ሚስት አገባሁ? ለምን ልጅ ወለድኩ? ከድሮው ኑሮየ ምን ቀለለኝ? ምንስ ተሻለኝ? ባሰብኝ እንጅ! ” (ፍቅ ም 2 ገጽ 22) እያሉ አቶ ቦግአለ ሙብራቱ ልጃቸው በዛብህ ጠፍቶባቸው ካናቡት እንባ የባሰ የኢትዮጵያውያን ወላጆች እንባ እየጎረፈ ነው፡፡

“አሁንስ ማየቱም መስማቱም ሰለቸኝ፡፡ አላይም ብየ ዓይኔን አልጨፍን፡፡ አልሰማም ብየ ጆሮየን አልዘጋ “የሰማዩን ገጽታ እናየለን ትላላችሁ የዘመኑን ምልክት መለየት አትችሉም”(ማቴ 16፡3) ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወቅሷልና በዘመናችን የሚካሄደውን ማየት አለብን፡፡ ካላየንና ካልሰማን ለጸሎታችን ምን አጀንዳ ይኖረናል? አድርግልን ብለን እንጸልያለን? ብለውኝ ተሰነባበትን፡፡

ካለፉት አምስቱ ወራቶች ወዲህ አቅም እያነሳቸው፡ ጆሯቸው እየደከመ፡ ቀጥታ ስደውልላቸው መመለሱን እየቀነሱ መጡ፡፡ ሊያነጋግሩኝ ሲፈልጉ የሚያገናኙኝ አቶ ገብርኤልና ሌሎች እህቶች ብቻ ሆኑ፡፡ ይህችን ዓለም ከለቀቁባት ከሚያዝያ 21 ቀን ቀደም ብለው ከሶስት ቀናት በፊት፡ በአቶ ገብርኤል በኩል አገኙኝና “እግዚአብሔር ይፍታሽ ብለህ አሰናብተኝ” አሉኝ፡፡ እኔም እናታችን አሁንማ ሁላችንን ያሰረችን ኮሮና ቫይረስ የምትባለው ከቁንጫ ያነሰች ኢምንት እሷው ትፋትን ብየ ቀለድኩባቸው፡፡ “ቀልዱን ተወውና እግዚአብሔር ይፍታሽ ብለህ አሰናብተኝ” አሉኝ፡፡

እኔም “ወንሕነኒ ናፍጥን ከመ ነሀሉ ውስተ ሃይማኖት ርትእት ወበከመ ጽሑፍ ወንሥራዕ አልባቢነ ከመ ንተሉ ስብሀተ ርቱዐ ዘረከቡ ዕልከቱ” (ሃይ ም 74፡7) እንዲል መጽሐፉ፡- እርሰዎ እኮ ወደ እግዚአብሔር ከኔ ይልቅ ቀድመውኝ ቀርበዋል አልኳሸው፡፡ እንኳን ለርሰዎ ለማነኛውንም ሰው ይህን ቃል ለማለት እየከበደኝ ነው፡፡ በምገኝበት ቦታ ሁሉ በጥጌ ሌላ ቄስ ካለ ቢያደርገው ደስ ይለኛል፡፡ ሌላ ቄስ ከሌለ ግን “በማወቅም ባለማወቅም በሰራነው ኃጢአት ከታሰርንበት እግዚአብሔር ሁላችንንም ይፍታን” ብየ እንጅ ራሴን ከህዝቡ ለይቼ እግዚአብሔር ይፍታችሁ ለማለት እየከበደኝ ነው” አልኳቸው፡፡ ቢሆንም ካህን ነህና ትእዛዙን ፈጽምና አሰናብተኝ” አሉኝ፡፡ “እንበለ ደዌ ወህማም፡ እንበለ ጻማ ወድካም፡ አመ ከመ ዮም፡ ያብጽሐኒ ያብጻህኪ በሰላም“ ብየ አመታዊውን መሰነባበቻ መነሻ አድርጌ እግዚአብሔር ይፍታሽ”

ካልኳቸው በኋላ፤ አቶ ገብርኤልን እየጠሩ “በመስመሩ አለህ? ትሰማኛለህ? በመስመሩ ላይ መኖሩን አረጋገጡ። አቶ ገብርኤልም ድምጹን ከፍ አድርጎ “እናታችን አለሁ እሰማለሁ” አላቸው። “ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ይባርክህ፤ ላደረክልኝ ሁሉ ዋጋህን ይክፈልህ” ብለው መረቁት። ቀጠሉና በምትቆዩባት ዓለም እግዚአብሔር ጠባቂያችሁና መሪያችሁ ይሁን” ብለው ሁላችንንም በማይደገም ስንብት ተለዩን። ከተሰነባበትን ከሶስት ቀናት በኋላ ሚያዝያ 14 ቀን አርፈው ሊቀማእምራን ዶክተር አማረ ካሣየ ማረፋቸውን አረዱኝ።

## ሠ. የወይዘሮ ውድነሽ ሞት ያስከተለብኝ ሶስት እዳወች

በቁመተ ሥጋ ያለ ወገን ለሞተ ወገኑ ተዝካር ፡ምሽና እንባ የሚከፍላቸው እዳወቹ ናቸው። ተዝካርን በማስቀደም ሁሉንም ባጫጭር አንቀጾች ለመግለጽ እሞክራለሁ።

### ተዝካር

ባለተዝካሩ ከተወለደ ጀምሮ ህብረተ ሰቡን ተለይቶ እስኪሞት፤ በህይወት በነበረባቸው ቦታወችና ወቅቶች በተግባር የፈጸማቸው በቃል የተናገራቸው በይፋ የሚነገሩበትና የሚሰሙበት በጥቅሉ ተዝካር ይባላል። ባለ ተዝካሩ በተግባር የፈጸመባቸው በቃል የተናገረባቸው ወቅቶችና ቦታወች ይጠቀሳሉ። ሰው የሚፈጽመው ተግባርና የሚናገረው ቃል ለሰው ከሰው ጋር ነው። የሰው አዕምሮ ተጽፎ ስለቀረበለት ብቻ ራሱ ያልትሳተፈበትንና በዓይኑ ያላየውን ጅል ካልሆነ በቀር ሳይጠራጠር ሁሉንም እንዳለ አይቀበለውም። ወይዘሮ ውድነሽን ከተደነቁባቸው ብዙ ነገሮች አንዱ የቀረበላቸውን ስርዝ ድልዝ እያረሙ መቀበላቸው ነው። ይህን የመሰለ የመታሰቢያ ጽሑፍ አቅራቢ፡ አንባቢንና ሰሚን ከጥርጥር ለመታደግ ከሚታሰበው ወገን ጋራ በተጠቀሱት ቦታወችና ወቅቶች የነበሩትን ሁሉ ሰዎች መጥቀስ አለበት።

ይህ ሁሉ ተሟልቶለት ከቀረበለት በኋላ፡ አንባቢና ሰሚ ሊማርበት፡ ሊደነቅበትና ራሱን ሊያዘጋጅበት ሲገባ እኔ በአካል ካልተሳተፍኩበትና ከሌለሁበት አልቀበልም። አላምንም። የሚል ከሆነ፤ ሰው መሆኑን የማያውቅ፡ ወይም ራሱን አምላክ ያደረገ ጅል ይባላል።

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ሲወለድ ቢኖርም፤ ለመወለዱ እርግጠኛ ሆኖ አምኖ የሚቀበለው፡ በሶስት ነገሮች ነው። 1ኛ ለራሱ ልደት ምስክር ለመሆን በቅቶ የሚወለድ አለመኖሩን ያረጋግጣል። 2ኛ ከማን እና የት መቼ እንደተወለደ ሌላው በሚነግረው እንደሚያምን እና መካድ እንደማይችል ይመለከታል። 3ኛ የራሱ ህልውና በዚህ መንገድ ብቻ እንደመጣ ያረጋግጣል። ከዚህ ሁሉ መረጃ አፈንግጦ መወለዱን ሊክድ አይችልም።

ሌላው ሞት ነው። ማንም ሰው መሞቱን ቀምሶና ሞክሮ ለራሱ ሞት ምስክር ሊሆን አይችልም። የራሱን ሞት አምኖ ሊቀበል የሚችለው ሌላው ሰው ሲሞትና ሲቀበር በሚያው ነው። ክርስቶስ ከወንጌሉ ጋራ ታሪኳ ይነገርላት ያለላት ማርያም እንተ እፍረትና ቅዱስ ጳውሎስም አደራ ያለላት ፌቤን በመካከላችን የሉም። ግን ወንጌሉን እና መልእክቱን ስናነብ ውለታቸውን እናስባለን። ክቡር ዶክተር አዲስም “ውለታዋን አልረሳውም” ያሉት እሳቸው በማይኖሩበት ዓለም መጽሐፉን የሚነበው ሁሉ እንዳይረሳቸው ነው።

የወይዘሮ ውድነሽን መታሰቢያ መሠረት ያደረኩት ራሳቸው ያረቀቁትን ፍቅር እስከመቃብር የሚባለውን መጽሐፍ ነው። ከደራሲው ከክቡር አቶ አዲስ ጀምሮ ፍቅር እስከመቃብር መጀመሪያ ያነበቡትና የተረኩት የሰሙት በአጸደ ነፍስ እንጅ በሕይወተ ሥጋ አሁን የሉም። ከመጀመሪያ ሲነበብ ሲታተም ያልነበሩ፤ እንዲያውም ብራናየ ሰብልየ እያለ ዘመኑ በፈቀደውና ትውልዱን ሊጥቅመው

በሚችልበት ወቅት እንደገና አስውቦ ያቀረበው ቴዲ አፍሮ ዛሬ አለ። እኔን ጨምሮ ከግማሽ ምዕት ዓመት በኋላ ሁላችንም አንኖርም። አባታችን አቡነ መቃርዮስ “ለኢትዮጵያውያት እኅቶችህ ትምህርት ይሆን ዘንድ፡ ቀድሞ ከነበሩት ዛሬም ካሉት ወደፊትም ታላላቅ ሥራ ከሚሰሩት አንዷ ብለህ ግለጻቸው” ያሉኝን ተከትየ “አማረም ከፋም ተዝካሬን አውጥቻለሁ” እንዲሉ፡- ወይዘሮ ውድነሽን ከሞላ ጎደል የገለጽኳቸው ይመስለኛል። ከዚህ ቀጥየ ለሞተ ወገን በቁመተ ሥጋ ባለ ወገን ወደ ሚከፍለው መስዋዕት ምሾንና እንባን ለመግለጽ እሞክራለሁ።

እንባና ምሾ በህይወተ ሥጋ ያለው ለሞተው ሰው የሚከፍላቸው እዳወች ናቸው። በቁመተ ሥጋ ያለ ሰው ለሞተ ወገኑ በረደህ ላልብስህ፤ ዘቀዘቀህ ላንተርስ፤ ራበህ ላጉርስህ ፤ ውሐ ጠማህ ላጠጣህ አይልም። የሚያቀርብለት ምርጫ ስሜትን አስገድዶና ሰውነትን ፈንቅሎ የሚወጣውን የማይጠጠውን እንባ ማፍሰስ ነው።

ይህችን ከንቱ ዓለም የለቀቁትን የናታችን የወይዘሮ ውድነሽን የሞትን ጥልቀት እንዳንተረጉምበት ወደ ባህርነት ከተቀየረው አእምሯችን የሚፈልቀው እንባ ዓኖቻችንን ይጋርዳል። አካላውያን ዓይኖቻችን በእንባ ሲሸፈኑ ፤ ዓይነ ህሊናችን በምሾ ይከፈታል። ምሾ በቃል አማካይነት ካንደበት ይፈልቃል። ምሾና እንባ ተፈጻጻሚወች ናቸው። እንባ ሰም፡ ምሾ ወርቅ ሆነው በመገጣጠም ለሞተ ሰው መስዋዕት ሆነው ይቀርባሉ። ለእናቴ ለወይዘሮ ውድነሽ አምሳሉ ምሾየንና እንባየን መስዋዕት አድርጌ ያቀረብኩት ግጥም ከዚህ በታች እነሆ !



<u>የምሾ ግጥም</u>

ሰወች ሲሞቱ አይታ በነጀዋር ሜንጫ
በደብሮች መቃጠል ሰው ሁሉ ሲንጫጫ
ታየች ስትመንን አልፋ በደምበጫ
ከመሰንበት መሞት ሆነ የሷ ምርጫ
መበላቱን ጠላች ቆማ በቁንጫ
ጠፋች ብትፈለግ በጎንቻ በሜጫ
ከእግር እስከ ራሷ ተከናንባ ቢጫ።
ብላ በመናገር ወስኛለሁ እኔ
በአዲስ አባ መኖር መሰለኝ ኩነኔ
ተውት ቤቴ ይፍረስ መረጠኩኝ ምናኔ
ስሟ ተቀይሮ ከሆነ ፍንፍኔ
በደብሬ አልቀበር አይግባ አስከሬኔ
መሆን መርጫለሁ አባ ዓለም ለምኔ።

ልቧ እየተከዘ መንፈሷ እየባባ
ብላ እያለቀሰች ወይ አዲስ አበባ
ተዋርዳ ስታያት በበቀለ ገርባ
ላትመለስ ሄደች እየረጨች እንባ
ሁሉም ከሆነ እንዲህ ትቢያና ገለባ
የሚታዘልበት ከፈለገ አንቀልባ
ልቅር እንደወጣሁ እሬሳየ አይግባ።
ፈረንጅ የጻፈውን የውጩን ሲያደንቁ
አንች የጻፍሽውን ለማንበብ ሲንቁ
አዬ ድንቁርና አለመሆን ብቁ
እንደ ድመት ጸጉር በሙብነን አለቁ።
እዚያው እርስ በርሳቸው ተናንቀው ይለቁ።
እንዳች ለመሆን ሴቱ ቢለካካ።
ማንም አልተገኘም አንችን የሚተካ
አንች ሴቱን ሁሉ ትበልጫለሽ ለካ
አንችን ለመሾናት ሴት ወንዱ ተነሳ
ሰብለን እንደሾኛት እንደ ጉዱ ካሳ
ሰብለ የተባልሽው ለካ አንች ነሽ እሳ።
ለኔና ለገብሬል የገርሽን ነገር
ለምን ትይናለሽ አይወሳ  ይቅር
ይደበቃል ብለሽ  ያንች ገድል  ምሥጢር።
ምን እንመልሳለን ለዘመዶቻችን
ስትጠፊ እያየን ከመካከላችን
እርም እንዳይሆንብን ዝም ማለታችን
መጮህ አናቆምም እስኪዘጋ አፋችን።
እኛ እናከብራለን ያአዲስን አደራ
እንድናስታውስሽ አብረን ከሱ ጋራ
አዝማሪ ቢረሳሽ ስምሽን ባይጠራ
መሬት ቀውጢ ሆኖ እስኪነሳ አቧራ
ናወድሳሻለን  ቆመን በየተራ።
ስምሽን ባይጠራ ወጋየሁ ንጋቱ
የዝናሽ ምስክር አይቀርም በከንቱ።
ከእግር እስከ ራሷ ቢጫ ልብስ አጥልቃ
የዝወትር ኩታዋን ቀሚሷን አውልቃ
ተፈላጊነቷን መወደዷን አውቃ
ከዘመድ አዝማዷ ከሰው ተደብቃ
ተሰወራ ጠፋች  በሌሊት ጨረቃ።
ቴዴ በህሊናው፤ አሻግሮ ያየሽ
አበባ ስትቀስሚ፡ ንቢቷን ሆነሽ
ሰብልየ ሰብልየ፡ ሰብለዓለም ያለሽ
ለአዲስ ዓለማየሁ ንቢቱ አንች ነሽ።
ማርና ወለላ ፡ ጧፍም ያመረትሽ።
ከወለላው ማርሽ የወጣው ሰፈፍ
ባአዲስ ዓለማየሁ ተደረገ ጧፍ

ወያኔ ለማጥፋት ቢያናፋ ወናፍ
ነበልባሉ ታየ ካጽናፍ እስካጽናፍ።
አዲስ ተነሳና በጨለማ ታጥቆ
የሚቀርጸው ብዕር ሲፈልግ ሸምበቆ
የፈጠረው አምላክ ፍላጎቱን አውቆ
አንችን ቀረጸለት እጅግ ተጠንቅቆ
በመገረም ሞተ ተደንቆ ተደንቆ።
ወረቀት ሲፈልግ ረፍዶ እስኪመሽ
አምላክ የራመመሽ ብራና አንች ሆንሽ።
ተለየሽኝ ብሎ አዲስ ሲወቅስሽ
ባለመከተልሽ በመዘግየትሽ
ተባበርሽው ዛሬ በመቃብርሽ።
የዲሲ ወይዛዝርት የተላቀሳችሁ
ውድነሽ አምሳሉ የሞተች መስሏችሁ
አለች አልሞተችም ተረጋጉ አይዟችሁ
ተሰወረች እንጅ አለች በውስጣችሁ
ታግሳችሁ ቆዩ እስከትጠራችሁ
ወደሷ ለመሄድ በየቀጠሯችሁ
ምንም ብትዘገዩ ታገኟታላችሁ።

በሕይወት ያለነውን ደቂቀ አዳምን እንደ እስስት እያነቀ ከሚገለው ኮሮና ቫይረስ ጋርዶና ጠብቆ በአካለ ሥጋ ያገናኘን። ከ አርባ ቀናት በፊት በሞት ከተለዩን ከናታችን ወይዘሮ ውድነሽና ቀደም ብለው ከዚህ ዓለም ከተለዩት ፍቅር እስከ መቃብርን ከደረሱት ከክቡር ዶ/ር አቶ አዲስ ዓለማየሁ፡ ካነበቡት፤ ከተረኩት ካአቶ ወጋየሁ ንጋቱ ጋራ እግዚአብሔር በሰማይ ያገናኘኝ።